District of Columbia
Office of the State Superintendent of Education

# የቤተሰብ መሳሪያዎች፣

## ውጤታማ የሆነ የትምህርት ቤት - የቤት ግንኙነት

ከልዩ ልዩ ህዝቦች ትምህርት እና ጥናት ማዕከል የተሻሻለ

http://www.cesdp.nmhu.edu/

## ማውጫ


አጠቃላይ ..... 3

የጥናት ምርምር ..... 3

አወንታዊ ማድረግ ..... 3

ሊተገበር የሚችል ማድረግ። ..... 3

ግላዊ ማድረግ ..... 3

ከመምህራን ጋር ያለ ግንኙነትን ለማሻሻል ያሉ ልምዶች ..... 4

የወላጅ/ቤተሰብ ግንኙነት ሀሳብ ..... 5

ለወላጆች የግንኙነት ሀሳቦች ..... 6

መሥፈርቶችን-መሠረት ያደረገ ትምህርትን መረዳት ..... 7

የትምህርት አስፈላጊነትን ለልጆች የማሳወቂያ መንገዶች ..... 8

ለወላጅ-መምህር ስብሰባዎች የእቅድ መመሪያ ..... 9

መማርን የሚደግፉ የቤት ውስጥ ልምዶች ..... 11

የተማሪን የርቀት ትምህርት መደገፍ ..... 12

## አጠቃላይ

ከልዩ ልዩ ህዝቦች ትምህርት እና ጥናት ማዕከልከተዘጋጁ ግብዓቶች የተሻሻለ፣ ይህ የቤተሰቦች ሰነድ ውጤታማ የትምህርት ቤት-የቤተሰብ ግንኙነት አስፈላጊነትን ይዳስሳል። ወላጆች፣ ቤተሰቦች እና መምህራን ስለ ትምህርት ቤት ፕሮግራሞች እና ፖሊሲዎች ፤ ስለ ተማሪ እድገት፣ የተማሪዎች ችግሮችን ስኬታማ በሆነ መልኩ እንዴት ምላሽ መስጠት እንደሚቻል እና ከትምህርት ቤቶች እና የማህበረሰብ **አባላት** ጋር ያለውን ግንኙነት እንዴት ማሻሻል እንደሚቻል ያላቸውን ግንዛቤ እንዲመረምሩ ተጋብዘዋል።

## የጥናት ምርምር

የጥራት ምርምር የመምህር-ወላጅ ግንኙነት ለተማሪ ስኬት ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ያመለክታል። *"መምህራን እና ቤተሰቦች በልዩ ልዩ ፤ ግልጽ እና ውጤታማ መንገዶች ስለትምህርት ቤት ፕሮግራሞች እና የተማሪዎች እድገት ሲገናኙ ግንኙነቱ ግልጽ ነው"። (Epstein, 1996)።* ተመራማሪዎቹ የቤተሰብ-ትምህርትቤት ግንኙነትን ለማሻሻል የሚከተሉ ስልቶችን ይመክራሉ፣

### አወንታዊ ማድረግ

- አወንታዊ ውጤቶች እና የተማሪ እድገትን መምህራን በየጊዜው እንዲያጋሩ መጠየቅ።
- ስለተማሪው ጥንካሬዎች እና ፍላጎቶች እንዴት ምላሽ መስጠት እንደሚችሉ መምህራንን እና ወላጆችን መጠየቅ።

### ሊተገበር የሚችል ማድረግ።

- ሥርዓተ-ትምህርቱን፣ ይዘቱን እና የቋንቋ መስፈርቶቹን ለመረዳት ግብዓቶችን መጠየቅ እና መፈለግ።
- ስጋቶችዎን ለወላጆች ወይም መምህራን ሲያጋሩ ግልጽ ይሁኑ።
- ወላጆች ፈታኝ በሆኑ ሁኔታዎች ተማሪያቸውን ለመርዳት ምን ማድረግ እንደሚችሉ ግልጽ ሀሳቦችን ይጠይቁ።
- ከወላጆች እና ተማሪዎች ጋር ስለ መማር ዓላማዎች እና እንዴት እንደሚፈተኑ ይነጋገሩ።

### ግላዊ ማድረግ

- ወላጆች የመምህራን ብቃቶችን የሚመለከት መረጃ መጠየቅ ይችላሉ።
- ስለሠራተኞች፣ፕሮግራሞች እና ጅምር ተሞክሮዎች እንቅስቃሴዎች የትምህርት ቤቱን ድረገጽ ይመልከቱ።
- ማንኛውም ጥያቄዎች፣ ስጋቶች እና አድናቆቶችን በአካል፣በኢሜይል፣በማስታወሻ እና በስልክ መግለጽ ይችላሉ።
- ወላጆች ስለልጃቸው የግል ፈተና ውጤቶች፣የምዘና መረጃዎች እና የስራ ናሙናዎችን በሚመለከት መረጃ መጠየቅ ይችላሉ።

## ከመምህራን ጋር ያለ ግንኙነትን ለማሻሻል ያሉ ልምዶች

እነዚህ ምክረሀሳቦች ውጤታማ የቤት-ትምህርት ቤት ግንኙነት ለመመስረት ይረዳዎታል። ተግባር ላይ ያዋሉትን ይምረጡ እና የቤት-ትምህርት ቤት ግንኙነቶችዎን ለመከታተል ዝርዝሩን በየሁለት ወራት ይመርምሩ።

| | |
|---|---|
| | • በትምህርት አመቱ መጀመሪያ ላይ እራስዎን ከልጅዎ መምህራን ጋር ያስተዋውቁ። |
| | • ከመማር ሂደቱ የሚጠበቁ አጠቃላይ ነገሮችን፣ምን ያክል የቤት ስራ ሊኖር እንደሚችል እና የሚሰጠውን ትምህርት እንዴት ማጠናከር እንደሚችሉ ይወቁ። |
| | • የወላጅ-መምህር ውይይት ማድረግ ካልቻሉ፣ወደ የሚመችዎ ቀን ወይም ጊዜ ቀጠሮውን ያስተላልፉ። |
| | • የልጅዎን መምህር በየጊዜው ያግኙ። |
| | • ወላጆች የተማሪው እድገት ላይ ለመወያየት ወይም የእድገት ሪፖርቶች ወደ ቤት እንዲላክላቸው ለማዘዝ ስልክ መደወል ይችላሉ። |
| | • አንድን ማስታወሻ፣የትምህርት ቤት ፖሊሲ ወይም ፕሮግራም ካልተረዱት፣ የትምህርት ቤቱ ሠራተኛ እንዲያብራራልዎ ይጠይቁ። |
| | • በትምህርት ቤቱ የሚላኩ የዳሰሳ ጥናቶችን ይሙሉ። |
| | • ስለትምህርት ቤቱ፣ዝግጅቶች እና ሠራተኞች የበለጠ ለማወቅ የትምህርት ቤቱን ድረገጽ በየጊዜው ይጎብኙ። |

## የወላጅ/ቤተሰብ ግንኙነት ሀሳብ

የትምህርት ቤት -ቤት ግንኙነትን ለመመዘን እና ግንኙነቱን ለማሻሻል ሊጠይቋቸው እና ሊወስዷቸው ስለሚችሏቸው ልዩ እርምጃዎች ለማሰላሰል ይህን ዝርዝር ይጠቀሙ።

| | **አልስማማም** | **በተወሰነ መልኩ እስማማለሁ** | **በጣም እስማማለሁ** | **ትምህርት ቤት የሚጠየቁ ልዩ ጥያቄዎች** | **ግንኙነትን ለማሻሻል የሚወሰዱ እርምጃዎች** |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. እኔ በመጽሄቶች፣ኢሜይል፣የቤት ውስጥ ጉብኝት፣የስልክ ጥሪ፣ ማስታወሻዎች፣ወዘተ፣በተለያዩ መንገዶች ከትምርህር ቤት መልእክት ይደርሰኛል። | ☐ | ☐ | ☐ | | |
| 2. እኔ ስለ ትምህርት ቤት ፖሊሲዎች እና አሰራሮች፣የስነምግባር ሂደቶች፣ የመመዘኛ መሳሪያዎች እና የትምህርት ቤት ግቦች ግልጽ መረጃ አገኝቻለሁ ወይም ጠይቄያለሁ። | ☐ | ☐ | ☐ | | |
| 3. እኔ ልረዳ በምችለው መንገድ እና ቋንቋ ከትምህርት ቤቱ መረጃ አገኛለሁ። | ☐ | ☐ | ☐ | | |
| 4. የወላጅ-መምህር ግንኙነት ከእኔ ፕሮግራም ጋር እንዲስማማ ተደርጎ የታቀደ እና የቋንቋ ፍላጎቶቼን የሚያሟላ እንደሆነ ይሰማኛል። | ☐ | ☐ | ☐ | | |
| 5. እኔ ስለ ልጄ ጥንካሬዎች፣የመማር ምርጫዎች፣ስጋቶች፣ባህርዮች እና ልጄን ስለሚያበረታቱ ነገሮች መረጃ አጋራለሁ። | ☐ | ☐ | ☐ | | |
| 6. እኔ ስለ ሥርዓተ-ትምህርት እቅዶች፣ የይዘት ደረጃዎች፣ከተማሪ ስለሚጠበቁ ነገሮች እና እንዴት መርዳት እንደምችል መረጃ ደርሶኛል ወይም ጠይቄያለሁ። | ☐ | ☐ | ☐ | | |

## ለወላጆች የግንኙነት ሀሳቦች

እነዚህ እርምጃዎች ከልጅዎ መምህራን እና የትምህርት ቤት ሠራተኞች ጋር ለመግባባት ያግዝዎታል። ሊያደርጓቸው የሚችሏቸውን ይምረጡ እና ከዚያ እድገትዎን ለማየት ከአንድ ወይም ሁለት ወር በኋላ ይህን ዝርዝር በድጋሚ ይመርምሩ።

| | | |
|---|---|---|
| ☐ | **ራስዎን ማስተዋወቅ** | በተቻለ መጠን በትምህርት አመቱ መጀመሪያ ላይ እራስዎን ከልጅዎ መምህር ጋር ያስተዋውቁ።<br>እርስዎ ተባባሪ ወላጅ እንደሆኑ እና በልጅዎ የመማር ልምድ ውስጥ መሳተፍ እንደሚፈልጉ ለመምህሩ ያሳውቁ። |
| ☐ | **እንግዳ አይሁኑ** | ወላጆች ጊዜ ወስደው ትምህርት ቤቱን ሲጎበኙ የድጋፍ መልእክት ያስተላልፋሉ።<br>ከትምህርት ቤቱ ሠራተኛ ጋር መደበኛ ግንኙነት እንዲኖርዎ ይጣሩ።<br>አልፎ አልፎ የመማሪያ ክፍሉን ለመጎብኘት፣ከልጅዎ ጋር ምሳ ለመብላት ወይም ትምህርት ቤቱ ውስጥ በበጎ ፍቃደኝነት ለመሳተፍ ከክፍሉ መምህራን ጋር ፕሮግራም ይያዙ።<br>ከልጅዎ መምህር ጋር በምናብ(ቨርችዋል) ለመገናኘት የቪድዮ ውይይት ይጠይቁ። |
| ☐ | **መነጋገር** | በትምህርት ቤቱ ውስጥ ስለሚከናወነው ነገር በየቀኑ ከልጅዎ ጋር ያውሩ። የመማሪያ ክፍሉን ቋንቋ ይማሩ እና ይህን ልጅዎን ስለውሎው/ሎዋ ለመጠየቅ ይጠቀሙበት። |
| ☐ | **ስብሰባዎች** | የወላጅ-መምህር ስብሰባዎች ላይ ይገኙ። በሌሎች የዓመቱ ጊዜያት ስጋቶች ወይም ጥያቄዎች ካሎት የውይይት ጊዜ ይጠይቁ። |
| ☐ | **መረጃ ያጋሩ** | ለልጅዎ ጠቃሚ ሆነው ያገኟቸው በቤትዎ ውስጥ የሚጠቀሟቸው የመማሪያ ዓይነቶች እና ስልቶችን በማሳወቅ የልጅዎን መምህር ይርዱት ወይም ይርዷት። በተጨማሪ፣የቤትዎን ቋንቋ ወይም ባህል ያጋሩ። |
| ☐ | **በሚስጥር ይጠይቁ** | ተማሪዎች ወላጆችን እና መምህራንን እንደ ተባባሪ ቡድን አድርገው መመልከታቸው ጠቃሚ ነው። ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች በወላጅ እና በመምህር መካከል በሚስጥር መታየት አለባቸው። ከመመህሩ ጋር እንደሚገናኙ ለልጅዎ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው። |
| ☐ | **የኢሜይል ጉብኝቶችን ይጠይቁ** | አንዳንድ ጊዜ የእርስዎ ፕሮግራም እና የትምህርት ቤቱ አይገናኙም። ኢሜይል ከትምህርት ቤት ሰራተኞች ጋር ለመገናኘት በጣም ውጤታማ መንገድ ነው። የቤት ኮምፒውተር ከሌሎት ኢንተርኔት ለማግኘት የአካባቢዎ ቤተመጽሀፍት ጋር ይሞክሩ። |
| ☐ | **አመለካከትዎን መጠበቅ** | አንዳንድ ጊዜ ወላጆች የትምህርት ቤት ጉዳዮችን እና ከልጃቸው ጋር ካላቸው ስሜታዊ ትስስር የተያያዙ ጉዳዮችን የመለየት ችግር ሊኖራቸው ይችላል። ያስታውሱ ትምህርት ቤቱ የእርስዎ አጋር መሆኑን፣እና በአወንታዊ መልኩ በመስራት፣ልጅዎ በሙሉ አቅሙ/ሟ ስኬታማ እንዲሆኑ ማገዝ ይችላሉ። |

## መሥፈርቶችን-መሠረት ያደረገ ትምህርትን መረዳት

እርስዎ ከተማሪ ስለሚጠበቁ ነገሮች እና መሥፈርቶችን- መሰረት ስላደረገ ትምህርት ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉት፣የሚከተሉትን ሀሳቦች እና ጥያቄዎችን እንደ መመሪያ ይጠቀሙ።

**1. መስፈርቶቹን በተሻለ መንገድ እንዴት መረዳት እንደሚችሉ ይጠይቁ። (WIDA, CCSS, NGSS...)**

- የመስፈርቶቹን ቅጂ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?
- ልጄ መማር የሚጠበቅበት ምንድን ነው?
- ልጄ የበለጠ ፈተና ወይም ድጋፍ የሚያስፈልገው ቢሆን ምን ላደርግ እችላለሁ?
- ልጄን እንዴት ማገዝ እችላለሁ?

**2. ትምህርት ቤትዎ መስፈርቶቹን እንዴት እንደሚጠቀም ይጠይቁ።**

- በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ ስለሚሰጠው ትምህርት እና እንዴት እንደሚሰጥ ውሳኔ የሚሰጠው ማነው?
- ልጄ WIDA እና/ወይም የጋራ ቁልፍ የስቴት መስፈርቶችን በሚመለከት እንዴት እየሰራ መሆኑን እንዴት አውቃለሁ?
- ልጄ በምን ያክል ጊዜ ይፈተናል?
- ልጄ የሚፈተናቸውን ፈተናዎች ውጤቶቹን እንዴት ላውቅ እችላለሁ?

**3. በትምህርት ዓመቱ መጀመርያ ላይ፣በትምህርት ይዘቶች እና የቋንቋ እድገት ላይ ከልጅዎ ምን እንደሚጠበቅ ይጠይቁ።**

- ልጄ በዚህ ዓመት በንባብ፣ ሂሳብ፣ ሳይንስ… ምን እንዲማር ይጠብቃሉ?
- በክፍልዎ ውስጥ ያሉ ልጆች በዚህ ዓመት ሊማሩት የሚገባ በጣም አስፈላጊ ነገሮች ምንድን ናቸው?
- እነዚህን ችሎታዎች ልጄ እንዲማር ለመርዳት በቤት ውስጥ ምን ማድረግ እችላለሁ?
- ልጄ ለቤት ሥራ በየቀኑ ምን ያህል ጊዜ መስጠት አለበት?
- በዚህ ዓመት ልጄ ምን ዓይነት የጽሑፍ ፕሮጀክቶች ይኖሩታል? በየትኛው ቋንቋ?

**4. በዚህ ዓመት፣ልጅዎ እንዴት እየሰራ መሆኑን ይከታተሉ።**

- የጋራ ቁልፍ የስቴት መስፈርቶችን በመጠቀም የልጄ ስራ እንዴት ይመዘናል?
- ልጄ በእንግሊዘኛ ቋንቋ እድገት ላይ እንዴት እየሰራ ነው?
- እድገት ለማሳየት የተለየ መስፈርትን(የውጤት መመሪያዎች፣ርእሶች፣ወዘተ) ይጠቀማሉ? ከሆነ፣የነሱን ቅጂ መውሰድ እችላለሁ?
- የእድገት ሪፖርት ለወላጆች በምን ያክል ጊዜ ነው የሚሰጠው?
- ልጄ የሚጠበቅበትን የ"ብቃት" ደረጃ ላይ መድረሱን እንዴት አውቃለሁ? ምን ማለት ነው?

## የትምህርት አስፈላጊነትን ለልጆች የማሳወቂያ መንገዶች

ልጅዎ ስኬታማ እንዲሆን ለመርዳት ማድረግ የሚችሉት ተመራጭ ነገር በሱ ወይም የሷ ትምህርት ላይ ሁሉ ጊዜ ፍላጎት ማሳየት እና የመማርን ደስታ መካፈል፣እንዲሁም ጥሩ የንባብ እና ጽሁፍ ልምዶችን ተሞክሮ ማድረግ ነው። በእውነቱ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ከሚያሳልፉት ጊዜ የበለጠ በቤት ውስጥ ብዙ ጊዜ ያጠፋሉ። ከትምህርት ቤት ውጭ ያለ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉበት መንገድ በትምህርት ስኬታቸው ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል።

ልጅዎ ስኬታማ እንዲሆን ለመርዳት ከእነዚህ ነገሮች ውስጥ የትኛውን ማድረግ ይችላሉ?

| | |
|---|---|
| ☐ | **ለልጅዎ ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን ያሳውቁት።**<br>• ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን እንዲያውቅ ከልጅዎ ጋር በየቀኑ ይስሩ።<br>• ዝርዝር ጥያቄዎችን ይጠይቁ፣ለምሳሌ "የሂሳብ ፈተናው እንዴት ነበር?" ወይም "የሳይንስ ሙከራዎ አስደሳች ነበር?"<br>• ምን ዓይነት ጥያቄዎችን መጠየቅ እንዳለብዎ ለማወቅ በመማሪያ ክፍል/ምናባዊ(ቨርችዋል) ትምህርት ውስጥ ስለተከናወኑ ዝርዝር ተግባራትን ይወቁ። |
| ☐ | **ስለ ልጅዎ ትምህርት ቤት የተቻለውን ያህል ይማሩ።** የልጅዎን መምህራን ይወቁ እና የልጅዎን ትምህርት መደገፍ እንደሚፈልጉ ያሳውቋቸው።<br>• የወላጅ-መምህር ስብሰባዎች ላይ ይገኙ።<br>• የትምህርት ቤቱን ድረገጽ ይጎብኙ።<br>• በትምህርት ቤቱ ውስጥ የወላጅ -መምህር ድርጅትን ይቀላቀሉ።<br>• የመማሪያ ክፍሉን ይጎብኙ፣ወይም ለትምህርት ቤቱ የተወሰነ የበጎ ፍቃደኝነት ተግባር ያድርጉ።<br>• ወደ ትምህርት ቤቱ መምጣት ለእርስዎ አስቸጋሪ ከሆነ፣ቤት ውስጥ እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ይጠይቁ ወይም የራስዎን ሀሳብ ያቅርቡ። |
| ☐ | **የልጅዎን ትምህርት ያስፋፉ** ነቅተን ያለንበት እያንዳንዱ ጊዜ የመማሪያ እድል ነው።<br>• ልጅዎ ቴሌቪዥን በመመልከት ወይም ቪዲዮ ጌም በመጫወት የሚያሳልፈውን ጊዜ ይገድቡ።<br>• ልጅዎ የሚያነብ የሚጽፍ መሆኑን እና እሱ ወይም እሷ እርስዎ ሲያነቡ እና ሲጽፉ ማየታቸውን ያረጋግጡ።<br>• ልጅዎ እሱ ወይም እሷ እንዲማሩ የሚረዷቸው ቦታዎች እንደ ቤተመፃህፍት፣ሙዚየሞች፣ መካነአራዊት(ዙ)፣ከቤት ውጪ ስፍራዎች፣የንግድ ቦታዎች እና ሌሎች ቦታዎች ይውሰዷቸው። |
| ☐ | **ልጅዎ በየቀኑ ለትምህርት ቤት መዘጋጀታቸውን ያረጋግጡ።**<br>• ልጅዎ ከመውጣቱ በፊት ጥሩ እንቅልፍ መተኛቱን እና ጤናማ ምግብ ማግኘቱን ያረጋግጡ።<br>• የተሰጠው የቤት ስራ እና የትምህርት ተግባሮች መጠናቀቃቸውን ለማረጋገጥ ከልጅዎ እና ከሱ/የሷ መምህር ያጣሩ። |
| ☐ | **ልጅዎን ያበረታቱ እና በማህበረሰብዎ ውስጥ ስላሉ በጎ አርአያዎች ያውሩ።**<br>• የኮሌጅ ድግሪ ወይም የሞያ ስራ ያላቸውን ሰዎችን እና ለአከባቢዎ ማህበረሰብ እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ይለዩ።<br>• ስለ ሙያ እና ምርጫዎች እና በትምህርት ቤት ውስጥ ጥሩ መስራት ከህይወት ምርጫዎች ጋር እንዴት እንደሚቆራኝ ያውሩ።<br>• ለባህልዎ፣ቅርስዎ እና ቋንቋዎ ዋጋ የመስጠትን አስፈላጊነት ያጠናክሩ፡፡ |

## ለወላጅ-መምህር ስብሰባዎች የእቅድ መመሪያ

የልጅዎን የወላጅ-መምህር ስብሰባ ላይ ከመገኘትዎ በፊት ይህንን ቅጽ ይሙሉ እና ወደ ስብሰባው ይዘውት ይምጡ።

**የወላጅ-መምህር ስብሰባ**

የልጁ ስም፣___________________________________ የወላጅ ስም፣___________________________________
የመምህር ስም፣_______________________________ የክፍል ደረጃ፣________________________
የስብሰባ ቀን፣_______________________________ ጊዜ፣________________________

**ማውራት የምፈልጋቸው ነገሮች**

1. የኔ ወንድ ልጅ/ሴት ልጅ ቤት ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ይሰሩታል ብየ የማስባቸው ነገሮች፣

2. የኔ ወንድ ልጅ/ሴት ልጅ ትምህርት ቤት ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ይሰሩታል ብየ የማስባቸው ነገሮች፣

3. ከመምህሩ ጋር መወያየት የምፈልገው አንዱ ጉዳይ፣

**ስለ ልጄ**

1. መምህሩ ሊያውቃቸው ይገባል ብየ የማስባቸው ስለልጄ ህይወት ጠቃሚ ነገሮች፣

2. ልጅዎን ይጠይቁ፣ ስለትምህርት ቤት ምን ትወዳለህ?

3. ስለትምህርት ቤት የማትወደው ምንድን ነው? መምህርህን እንድጠይቀው ወይም እንድነግረው የምትፈልገው ማንኛውም ነገር አለ?

4. ያለኝ አንድ ጥያቄ ወይም ስጋት፣

እነዚህን ከመመህሩ ጋር ያጋሩ።

| ስብሰባው ላይ |
| --- |
| 1. ልጄ በንባብ፣ጽሁፍ እና ሂሳብ በሱ/በሷ የክፍል ደረጃ ላይ ናቸው?<br><br>2. በክፍል ውስጥ የልጄ ጥንካሬዎች ምንድን ናቸው?<br><br>3. በክፍል ውስጥ የልጄ ድክመቶች ምንድን ናቸው?<br><br>4. በክፍልዎ ውስጥ ካሉ ልጆች ምን ይጠብቃሉ(ባህርይ፣የስራ ልምዶች፣ወዘተ)?<br><br>5. ልጄ እስካሁን ያሳካቸው መለኪያዎች እና መስፈርቶች የትኞቹ ናቸው?<br><br>6. ትምህርት ቤት ውስጥ ልጄ ውጤታማ እንዲሆን እንዴት መርዳት እንዳለብኝ ጥያቄዎች ወይም ሀሳቦች ከፈለግኩኝ እርስዎን እንዴት ማግኘት እችላለሁ? |
| ከስብሰባው በኋላ |
| 1. ስለ ወላጅ-መምህር ስብሰባው ከልጅዎ ጋር ያውሩ። የልጅዎን ጥንካሬዎች ያድንቁ።<br><br>2. ስለልጅዎ አንድ ዓቃፊ(ፎልደር) ያዘጋጁ። በዚያ ውስጥ የሚከተለውን ያካትቱ፣<br>• ሪፖርት ካርዶች<br>• የስራ ናሙናዎች<br>• የመምህሩ ማስታወሻዎች<br>• የፈተና ውጤቶች<br><br>3. የቀን መቁጠሪያ(ካላንደር) ያዘጋጁ እና የሚከተሉትን ምልክት ያድርጉ፣<br>• ስብሰባዎች<br>• አስፈላጊ ዝግጅቶች<br>• በልጅዎ ትምህርት ቤት ውስጥ ማህበራዊ ዝግጅቶች<br><br>4. የልጅዎን የክፍል ስራ እና የቤት ስራ በየቀኑ ያረጋግጡ።<br><br>5. የልጅዎን እድገት ለመወያየት ከመምህሩ ጋር መነጋገርዎን ይቀጥሉ። |

## መማርን የሚደግፉ የቤት ውስጥ ልምዶች[1]

ጤናማ የሆኑ የእለት ተለት ተግባሮች ተማሪዎች ወደ የርቀት ትምህርት እንዲሸጋገሩ ሊረዳ ይችላል፣ እና ቤተሰቦች እነዚህን የእለትተለት ተግባሮችን በማዘጋጀት እና በመጠበቅ ተማሪዎቻቸውን ሊረዱ ይችላሉ። በቤት ውስጥ ቀጣይነት ያለውን ትምህርት የሚያበረታታ የትምህርት አካባቢ ለማዘጋጀት ይህን ዝርዝር ይጠቀሙ።

| | |
|---|---|
| ☐ ሁል ጊዜ<br>☐ አንዳንድ ጊዜ<br>☐ መቼም | **የጊዜ ሰሌዳ ያዘጋጁ።** አብዛኛው ልጆች በትምህርት ቤት የጊዜ ሰሌዳ ለምደዋል፣ ተመሳሳይ አይነት ነገር በቤት ውስጥ መፍጠር ወደተለየ አይነት የትምህርት አካባቢ ያለውን ሽግግር ሊያቀል ይችላል። ከልጅዎ መምህር የጊዜ ሰሌዳውን እና የኦንላይን ክፍለጊዜዎች ቀን እና ጊዜን ይጠይቁ። |
| ☐ ሁል ጊዜ<br>☐ አንዳንድ ጊዜ<br>☐ መቼም | **እረፍቶችን ያዘጋጁ።** የማህበራዊ ርቀት ምክረሀሳቦችን ተከትለው የአካል እንቅስቃሴዎችን እና ከቤት ውጪ ጊዜን ለማበረታታት የተወሰነ ዓይነት የእረፍት ጊዜን ያካትቱ። ከቤት ውጪ ጊዜ እና ንጹህ አየር ትልቅ አካላዊ እና አእምሯዊ ጥቅሞች አላቸው። |
| ☐ ሁል ጊዜ<br>☐ አንዳንድ ጊዜ<br>☐ መቼም | **የእደጥበብ ይኑሮት።** የአርት(ሥነ ጥበብ) ፕሮጀክቶችን ለመፍጠር ቤት ውስጥ በቀላሉ የሚገኙ ግብዓቶችን መጠቀም። አርት(ሥነ ጥበብ) የትምህርት አስፈላጊ አካል ነው። በቤት ውስጥ አርት(ሥነ-ጥበብ) መፍጠር ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር ጥራት ያለው ጊዜን እና ከባህላቸው ጋር አግባብነት ያላቸውን ወጎች እንዲጋሩ እድል ይሰጣቸዋል። |
| ☐ ሁል ጊዜ<br>☐ አንዳንድ ጊዜ<br>☐ መቼም | **የእንቅልፍ ጊዜን ያክብሩ።** ልጅዎ ጤናማ የእንቅልፍ ልምዶችን እንዲኖረው እና የቪዲዮ ጌም(ጨዋታዎችን) እየተጫወተ ወይም ከልክ ያለፈ ኤሌክትሮኒክስን እየተጠቀመ በተለይም በምሽት ዘግይቶ እንዳይተኛ ያበረታቱት። |

[1] ለLEA እና ቤተሰቦች የOSSE የርቀት ትምህርት ግብዓቶችhttps://osse.dc.gov/distancelearning

## የተማሪን የርቀት ትምህርት መደገፍ

ልጅዎ ምን እንደሚሰራ፣እንደሚማር እና እንደሚለማመድ በማወቅ የቤተሰብ **አባላት** የተማሪውን የርቀት ትምህርት መደገፍ ይችላሉ። ውጤታማ የቴክኖሎጂ መሣሪያዎች አጠቃቀም እና ጥራት ያላቸው የኦፍላይን እንቅስቃሴዎች የተማሪው ወደ ምናባዊ(ቨርችዋል) ወይም ድብልቅ የማስተማር ሁኔታ ሽግግር ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አላቸው። ልጅዎ ለርቀት ትምህርት ዝግጁ መሆኑን ለማረጋገጥ ይህንን የዝርዝር እንደ መመሪያ ይጠቀሙ።

| |
|---|
| **1. ከልጅዎ ትምህርት ቤት እና መምህር ጋር ያሎትን ግንኙነት ይጠብቁ።** |
| ☐ ስለ አሰራሮች፣የኦንላይን ትምህርት፣ቀኖች እና ጊዜዎች የልጅዎን ትምህርት ቤት ወይም መምህር ይጠይቁ።<br>☐ የኦንላይን ትምህርቱን ለማግኘት በይነገጽ፣የተጠቃሚ ስም እና የይለፍ ቃሉን ይለዩ።<br>☐ የልጅዎን መምህር ኢሜይል፣የስልክ ቁጥር ወይም ያላቸውን ሌላ የመገናኛ ዘዴ(ቻነል) ይኑሮት። |
| |
| ☐ ለልጅዎ ጆርናል ወይም ማስታወሻ ደብተር ይስጡ።<br>☐ ልጅዎ የሚጽፍበት፣የሚነድፍበት ወይም የሚስልበት ቦታ እና ጊዜ ይስጡ።<br>☐ እያንዳንዱ ሰው ስለሚሰማው ስሜት ለማውራት የቤተሰብ ጊዜ ያዘጋጁ። |
| **3. የልጅዎን ስራ ያረጋግጡ።** |
| ☐ በተማሪው በራሱ ጥረት የሚጠናቀቁ የቤት ስራዎች፣የውይይት ቦርዶች፣ፎረሞች፣እና ፕሮጀክቶች ማወቅዎን እና መረዳትዎን ያረጋግጡ።<br>☐ ለልጅዎ የተሰጡትን የትምህርት ሥራዎችን ለማጣራት በቀን ውስጥ አንድ ጊዜ ይመድቡ።<br>☐ ምን ዓይነት የትምህርት ይዘት እና/ወይም የትምህርት ስራዎች እንደተሰጠ ተነጋገሩ።<br>☐ ልጅዎን የሱ/የሷ ተወዳጅ ተግባር ምን እንደሆነ እና ለምን እንደሆነ ይጠይቋቸው።<br>☐ ልጅዎን ለመስራት የትኛው ስራ አስቸጋሪ እንደሆነ እና በምን ምክንያት እንደሆነ ይጠይቋቸው። |
| **4. የትምህርት ተግባሮችን ለማጋራት ከልጅዎ ጋር ግልጽ እና ወጥ የማያቋርጥ ግንኙነት ይመስርቱ።** |
| ☐ ሁሉጊዜ ከልጅዎ ጋር ለማውራት የበለጠ ምቾት የሚሰጦትን ቋንቋ ይጠቀሙ። እርስዎ ለመርዳት እንግሊዘኛ መናገር አይጠበቅብዎትም።<br>☐ ጮክ ብለው ያንብቡ እና ስለጽሁፉ የሚያስቡትን ነገር ይግለጹ።<br>☐ ቀን ላይ ምን እንደሚያደርጉ ይግለጹ እና እሱ/እሷ ምን እንደሚያደርጉ እንዲገልጹ ልጅዎን ይጠይቋቸው።<br>☐ ቤት ውስጥ አንድ ምግብ እንዴት እንደሚሰራ ወይም አንድ ነገር እንዴት እንደሚጠገን ያለውን ሂደት ደረጃ በደረጃ  በሂደት ይግለጹ።<br>☐ ልጅዎን የቤት እንሥሣትን በመንከባከብ፣ለእራት ጠረጴዛውን ማዘጋጀት ወይም ሌሎች የቤት ውስጥ ስራዎች ላይ ያካትቷቸው። |